*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ሐሙስ፣ ነሃሴ ፲፪፣ ፪ሺ ፲፬ ዓ.ም. (Aug. 18, 2022)* *ቅጽ ፱ ቁጥር ፷*

# መተባበር ለአንድ አገር!

## የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የጉራጌ ማህበረሰብ ወገኖቻችን የሚያደርጉትን የህልውና ማስከበር ትግል ከልብ ይደግፋል።

ከቀናት በፊት የጉራጌ ማህበረሰብ ከወረዳ ወደ ክልል የመሆን ሕገመንግሥታዊ መብቱ የሚፈቅድለትን ጥያቄውን በሥልጣን ላይ ያለው ተረኛ ቡድን እንደለመደው ለራሱ ፍላጎት አመች በሆነ መልኩ አወሊጋግዶ የሕዝቡን የተባበረ ጥያቄና አንድነት በኃይልና ባሻጥር አናግቶ በራሱ መልክና ከመዋጥ ዓላማ አንጻር በሚያመቸው መንገድ ለመመለስ መሞከሩን የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ያወግዛል።

የጉራጌ ማህበረሰብ እንደ ዐማራውና ሌላው አገር ወዳድ በኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት ላይ የማይደራደር፣ ለነጻነቷና ለሕዝቡ ሰላምና አብሮነት በክፉና መልካም ጊዜ አብሮ የቆመና ሁሉንም የተካፈለ፣ የተዋለደ ሕዝብ በመሆኑ ብሎም በአገር አፍራሾቹ ዓይን ከዐማራው ማህበረሰብ ተነጥሎ የማይታይ ጠላት ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ ጥያቄው የመላው ዐማራም ጥያቄ ነው እንላለን። ምንም እንኳን የክልል ጥያቄና አደረጃጀት ሥርዓቱ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሕዝቡን በጎሳ ለያይቶ እርስበርሳችንን ለማባላት አቅዶ የወጠነው ክፉና መርዘኛ አደረጃጀት መሆኑን ብናውቅም አስተዳድርበታለሁ የሚለውን የራሱን ሕግ ጥሶ ለአንዱ የሚፈቅደው ለሌላው የሚነሳው መብት ማድረጉ በምንም አንጻር ቢሆን ተቀባይነት የለውም።

የጉራጌ ወገኖቻችንም ሆኑ ሌሎቹ ክልል በመሆን የዴሞክራሲ፣ የእኩልነትና የአገር ባለቤትነታቸው ጥያቄ ይመለሳል ማለት እንዳልሆነ የክልል ባለቤት ከሆነውና ለብዙ መከራና ግፍ እንዲሁም ጭፍጨፋና መፈናቀል ከተጋለጠው ከዐማራው ወገናቸው ትምህርት ሊቀስሙ ይችላሉ ብለን እናምናለን። ስለሆነም የመብትን ልክ ለማሳዬት ካልሆነ በቀር የጉራጌ ማህበረሰብ እንደ ዐማራው ወገኑ የክልል ባለቤት ቢሆን ከችግር ተላቀቀ ማለት እንዳልሆነ ተረድቶ ሁሉም ዜጋ የሚያምርበት በኢትዮጵያዊነት መቆሙና የልዑላዊት አገር ባለቤት ሆኖ ከክልል አጥር ወጥቶ እንደቀድሞው በነጻነት በፈለገበት ቦታ ሄዶ ሠርቶ ማደር ለሚችልበት አገራዊ አወቃቀርና ሥርዓት በጋራ መታገል ለሁሉም ዜጋ የተሻለና ትክክልም ነው እንላለን።

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የአሁኑን የጉራጌ ማህበረሰብ የትግል አንድነት እያደነቀ በሰርጎ ገቦችና በአድርባዮች ሳይጠለፍ በትግሉ እንዲቀጥልበት ያሳስባል። በሸርፍራፊ ጥቅም ተደልለው ትግሉን ለማኮላሸት የሚሞክሩ ቢኖሩ በንቃት ሊከታተላቸው ይገባል ። ይህ ትግል ለታላቁ አገራዊ ትግል የመንደርደሪያና የዐማራውና የጉራጌው ማህበረሰብ ብቻም ሳይሆን የሁሉም አገር ወዳድ ማህበረሰብ የተቀናጀና የተባበረ ትግል መሠረት ይሆናል ብለን እናምናለን። ስለሆነም የዐማራው

ማህበረሰብ ምንጊዜም ከጎናችሁ እንደሚቆም ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ያረጋግጣል። የጉራጌ ማህበረሰብም ከዐማራው ወገኑ ጋር የጠበቀ የትግል አጋርነቱን በተግባር እንዲያሳይ በትህትና እንጠይቃለን።

በአሁኑ ጊዜ በብዛት የዐማራውና የጉራጌው ተወላጅ ለዘመናት የኖረባትና የሚኖርባት፣ ሃብት ንብረት ያፈራባትና የገነባት አዲስ አበባ በትልቅ አደጋ ላይ ስለምትገኝ ከተማዋን ከጥፋት ለማዳንና እራሱንና ታሪኩን ብሎም ቀጣዩን ትውልድ የአገሩና የከተማዋ ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ ነቅቶ መጠበቅና ያንዣበበውን አደጋ ከሥሩ መንጥሮ ለመጣል መመካከርና መዘጋጀት ወቅቱ ነው እንላለን።

ኢትዮጵያ አገራችን በተባበሩ ልጆቿ ትግል፣ በአገር ጠሎቹ የተደቀነባትን አደጋ ትሻገራለች!

ድል ለአገር ወዳዶቹ የዐማራ፣የጉራጌና ሌሎቹም ማህበረሰቦች ይሁን!! አንድነታችን ይጠንክር!!